# ነጻ የተመራማሪዎችና የምርምር ህትመት ተሳታፊዎች መለያ ቁጥር (ORCID) አስፈላጊነት፣ ማወቅ ያለብን ቁልፍ ነገሮች እና አጠቃላይ መረጃ


## አዘጋጆች

ዶ/ር ሃይሉ ክንዴ አዲስ
ፕሮፌሰር ይኽነው ገ/ሥላሴ መንገሻ
ሙሉጌታ አለማየሁ አድማሱ
ላቀ መኩሪያው አለሙ
አዳነ ካሴ ቸኮለ




## ሀ: ORCID ምንድን ነው?

Open Researcher and Contributor ID (ORCID) ለተመራማሪዎች፣ ለአርታኢዎች፣ ለሳይንሳዊ ጽሁፍ አዘጋጆች፣ ወይም በዘርፉ ለተሰማሩ ባለሙያዎች የሚሰጥ ነፃ፣ ልዩ ባለ16 አሃዝ ሲሆን፣ ቋሚ እና ዓለም ዓቀፋዊ ዲጂታል መለያ ቁጥር ነው። ይህ መለያ ቁጥር የስም ተመሳሳይነትን በመከላከል የምርምር ውጤቶችም በትክክል በእርስዎ ስም እንዲመዘገቡ ይረዳል። በትምህርትና በምርምር ዓለም ውስጥ ያሉዎትን ሁሉንም ስራዎች (የምርምር ጽሁፎች፣ መጽሐፍት፣ ፕሮጀክቶች፣ የሚሰሩበት ተቋም ወዘተ) በትክክል ለማመላከትና ለማስተሳሰር መለያ ቁጥሩ ይጠቅማል። በተጨማሪ ስምዎን፣ ስራዎን፣ ተቋምዎን ወይም ዜግነት ቢቀይሩ የORCID መለያ ቁጥርዎ አይቀየርም (ለሕይወት ዘመን ይቆያል)።

ምሳሌ ORCID መለያ ቁጥር:
“https://orcid.org/0000-0003-0265-0261”

## ለተጨማሪ መረጃ:

- ✓ ድህረ-ገጽ፡ [orcid.org] (https://orcid.org)
- ✓ የመረጃና ድጋፍ ማዕከል፡ [support.orcid.org] (https://support.orcid.org)
- ✓ በሶሻል ሚዲያ፡ @ORCID_Org

ይህን ብሮሸር በዩኒቨርሲቲዎች፣ በምርምርና በሌሎች ተመሳሳይ ተቋማት ማሰራጨት ይቻላል።

## ምስጋና


በ7ኛው ዙር ORCID ግሎባል ተሳትፎ ፈንድ በኩል ለተደረገልን የበጀት ድጋፍ ምስጋናችንን እናቀርባለን።


## አድራሻ


አማራ ግብርና ምርምር ኢንስቲትዩት
ፖስታ ሳጥን ቁጥር፡ 527
ስልክ ቁጥር: +251 058 220 64 00
ፋክስ (FAX): 058 226 6077
EMAIL: ARARI@ARARI.GOV.ET
WEBSITE፡ WWW.ARARI.GOV.ET
ባህር ዳር- ኢትዮጵያ


## የመረጃ ማዕከል

helpdesk.orcid@arari.gov.et

## ለ: የORCID ዋና ጠቀሜታዎች

1. የስም ግራ መጋባትን ያስወግዳል፡፡ በዚህም ምክንያት የተመራማሪዎችን ስም በግልጽ እና በትክክል ይለያል፡
   - ✓ ከሌሎች ተመራማሪዎች ጋር ስምዎ ተመሳሳይ በመሆኑ ምክንያት፣ የትኛው ስራ የማን እንደሆነ ግራ የመጋባትን ችግር ይቀርፋል፡፡
2. ሁሉም የምርምር ስራዎን/ህትመተዎን በአንድ ቋት ለማስቀመጥ ያግዛል፡፡
   - ✓ የተለያዩ የህትመት አይነቶችን (ጆርናሎች፣ መጽሐፍትና ምዕራፎች፣ ወዘተ)፣ ግምገማዎች፣ ሽልማቶችን እና መረጃዎችን በአጭርና በተዋቀረ መንገድ ለማደራጀት ይጠቅማል፡፡
3. ግራንት እና የምርምር ማመልከቻዎችን ለመስራት ያግዛል፡፡
   - ✓ በማመልከቻ ቅጾች ላይ ብዙ ጊዜ የሚፈለገውን ዝርዝር ሁኔታ መሙላት ሳያስፈልግ ለORCID አድራሻዎን መስጠት ብቻ በቂ ይሆናል፡፡ በምርምር ህትመት፣ በፕሮጀክት እና በግራንት ማመልከቻ ሂደት ወቅት የሚፈጀዉን ጊዜ ይቀንሳል፡፡
4. የምርምር ውጤትዎ ዓለም አቀፍ ተደራሽነቱ ይጨምራል፡፡
   - ✓ በሺዎች የሚቆጠሩ ዩኒቨርሲቲዎች፣ የምርምር ተቋማት፣ የመጽሔት አዘጋጆች እና የገንዘብ አቅራቢ ድርጅቶች ከORCID ጋር ይሰራሉ፡፡ ይህም ምርትዎ/አገልግሎትዎ በዓለም አቀፍ ደረጃ እንዲታወቅ ያደርገዋል፡፡
5. የምርምር ስራዎን ተጽዕኖ ፈጣሪነት ያሳድጋል።

የታተሙ ስራዎችዎ በሌሎች ምሁራን ስንት ጊዜ እንደተጠቀሱ (Citation) በተዘዋዋሪ ማየት ይችላሉ፡፡

## ሐ: ORCID መለያ ማን ሊኖረው ይገባል?

- ✓ ተመራማሪዎች እና ሳይንቲስቶች
- ✓ የዩኒቨርሲቲ መምህራን እና ተማሪዎች (ማስተርስና ዶክትሬት)
- ✓ የመጽሔት አርታኢዎች እና ገምጋሚዎች
- ✓ የምርምር ፕሮጀክት መሪዎች
- ✓ የግራንት እና ስራ ፈላጊ አመልካቾች፡፡

## መ: በORCID መለያ ምን ማገናኘት ይቻላል?

- ✓ የታተሙ የመጽሔት ጽሁፎች
- ✓ በሂደት ላይ ያሉ ማንስክሪፕቶች
- ✓ የምርምር ፕሮጀክቶች እና የገንዘብ ድጋፎች
- ✓ የተቋም ትስስሮች (Affiliations)
- ✓ የግምገማ እና የአርትዖት ተሳትፎ
- ✓ የመረጃ ስብስቦች (መጻሕፍት፣ የኮንፈረንስ ጽሁፎችና ወዘተ)፡፡

## ሠ: ORCID አድራሻ እንዴት መፍጠር ይቻላል?

1. ወደ ድህረ-ገጹ ይሂዱ፦ [orcid.org] (https://orcid.org)
2. "Register now" ወይም "አዲስ አካውንት ይፍጠሩ" የሚለውን ይጫኑ፡፡
3. መሠረታዊ መረጃዎን ያስገቡ፦ ሙሉ ስም፣ የኢሜል አድራሻ (የሚጠቀሙትን)፡፡
4. የይለፍ ቃል ይፍጠሩ (ጠንካራ የይለፍ ቃል ቢሆን ይመከራል)፡፡
5. ተጨማሪ መረጃ (አማራጭ) ማለትም አጭር የስራ ለምድ፣ ሙያዊ ተሳትፎ፣ የትምህርት ደረጃ፣ የምርምር ህትመቶች፣ ሽልማቶችን ማስገባት ይችላሉ፡፡
6. ኢሜልዎን ያረጋግጡ፦ ወደ ኢሜልዎ የመጣውን አገናኝ በመጫን መለያዎን ያስገቡት፡፡
7. አዲስ የORCID ቁጥርዎን (ለምሳሌ፦ 0000-0001-2345-6789) ያገኛሉ!

መመዝገቡ ከ1 ደቂቃ በላይ አይወስድም!!

## ረ: መለያዎን ከፍ እንዴት ማድረግ ይቻላሉ? (መሙላት)

ባዶ መለያ ማግኘት ብቻ አይበቃም፤ ስራዎችዎን በሙሉ ወደ ORCID ገጽ ማስገባት አለብዎት፡፡
በORCID የመለያ ይግቡ፡፡

1. "Add Works" (ስራዎችን ጨምር) የሚለውን ይፈልጉ፡፡
2. ስራዎን ለማካተት / ለማስገባት 3 መንገዶች አሉ፡
   1. በድረ-ገጽ ላይ በመፈለግ ቀጥታ ማያያዝ፡ "Search & Link" በማለት ከPubMed፣ CrossRef፣ Google Scholar ወዘተ ስራዎን በራስዎ ስም ያገኛሉ፡፡ (በጣም ቀላል!)
   2. በእጅዎ አንድ በአንድ በማስገባት (የጽሁፉን ርዕስ፣ ደራሲዎች፣ ዓመት ወዘተ)
   3. በፋይል መጫን፡ BibTeX ወይም ሌላ ተመሳሳይ የፋይል አይነት ይጠቀሙ፡፡

## ሰ: ORCIDን በተግባር እንዴት እንጠቀማለን?

- ✓ ጽሁፍ ወደ ጆርናል ህትመት ስናመለክት
- ✓ በCV፣ በኢሜይል ፊርማ እና በድረ-ገጽ ላይ
- ✓ በፕሮጀክት እና በግራንት ማመልከቻ ወቅት

## ሸ: ORCID እና የምርምር ሥነ-ምግባር

ORCID ለምን ለምን ይረዳል፦

- ✓ በምርምር ውጤቶች ላይ ግልጽነትን ለማስፋፋት፣
- ✓ ትክክለኛ የጽሁፍ ወይም የአርትኦት ባለቤትነትን ለማረጋገጥ፣
- ✓ የሳይንስ ስርዓትን ታማኝነት ለማጠናከር፡፡

## ቀ: ዋና መልዕክት

አንድ ተመራማሪ — አንድ ORCID መለያ — የሕይወት ዘመን ዕውቅና

**በአጠቃላይ የORCID ዋና መርህ**: አንድ ጊዜ ያስገቡ፣ ለብዙ አገልግሎቶች ይጠቀሙበት (Enter once, reuse often)